የሰ/መ/ቁ. 48693

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-**ነኢማ አወል

**ተጠሪ፡-** የገቢዎች እና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ኃ/ስላሴ ገ/መድህን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መሰረት የሆነው ጉዳይ የጉምሩክ አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተውን የወንጀል ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰችው በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ስትገባ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸው የተለያዩ የሞባይል መለዋወጫዎችን እና የተዘጋጁ አልባሳቶችን ይዛ ተገኝታለች ተብላ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ በአቃቤ ሕግ ክስ የተነገረውን ወንጀል አልፈጸምኩም በማለት በመከራከርዋ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኂላም አመልካች ልትከላከል ይገባል በማለት ብይን በመስጠት የመከላከያ ማስረጃዋን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ጥፋተኛ መሆንዋን በማረጋገጡ ይዛው የተገኘችው እቃ እንዲወረስ፣በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በሚያህል የገንዘብ መቀጮ ብር 114,076.46(አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ሰባ ስድስት ብር ከአርባ ስድስት ሳንቲም) እንድትከፍል እና በሁለት ዓመት እስራት እንድትቀጣ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የተከሰሰችበት የወንጀል ድርጊት መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሰረት ነው ወይንስ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ፣እንደዚሁም የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 42753 እና 43806 ከሰጣቸው ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙትና በመጨረሻም ውሳኔ የሰጡት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ከፍ ሲል በተጠቀሱት መዝገቦች ተመሣሣይ አቤቱታ ቀርቦለት በእርግጥም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የጉምሩክ አዋጅ አንደሆነ በመግለጽ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ነው በሚል የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐአል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ይኸው ቀደም ሲል የተሰጠው የሕግ ትርጉም አስገዳጅነት ያለው ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 139937 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79028 ነሐሴ 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ(2) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ